# የወቅቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ፥ ማህበራዊ፥ ኢኮኖሚያዊ፥ ዲፕሎማሲያዊና ሌሎችም ተዛማጅ ሁኔታዎች

## ክፍል ሁለት

በክፍል አንድ ስለሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታና በአሁኑ ወቅት ስላለው እንቅስቃሴ፣ ስለ ኢኮኖሚ ልማትና ዕድገትም ሆነ ስለማኅበራዊ ችግሮች መወገድ ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ከመግባታችን በፊት የመሠረታዊ ጉዳዮች ተዛማጅነት ትስስርና ቁርኝትን መገንዘብ እንደሚያስፈልግ በማስረገጥ ነበር ዝግጅታችንን የቋጨነው:: መሠረታዊ የሆኑት ችግሮቻችን ጠንካራ ቁርኝት ስላላቸው ሌሎችን ተዛማጅ የሆኑትን አብረን ሳንዳስስ አንደኛውን ብቻ ለመፍታት መሞከር የሚፈለገውን ዕድገትና ልማት እንደማያስገኝልንም ገልፀን ነበር :: የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ከምንምና ከማንም በፊት በቅድሚያ የሕዝብን፥ ማለትም የሰው ሃይልን፥ ወሣኝነት መረዳት ተገቢ መሆኑን አጥብቆ ያምናል:: ስለሕዝብ ወሣኝነት ሲነሳ ደግሞ ብዛቱን ወይንም ቁጥሩን ብቻ ሣይሆን እንዲያውም ይበልጡኑ የዚህን ሕዝብ ጤናማነት፥የዚህን ሕዝብ በቂ ምግብና፥ በቂ ህክምና ማግኘት መቻሉን ማረጋገጥ ማለታችን ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ከሕዝቡ በአምራችነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘው ክፍል የተማረ ፥ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የሠለጠነ፣ ለሚጠበቁበት የልማትና ዕድገት ሥራዎች በቂ ዕውቀት ያለው መሆኑን ማሟላትን ይመለከታል:: በአንድ ሀገር ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ልማት እንዲመጣ ያለጥርጥር በዚያ ሀገር ውስጥ ሠላም እንዲኖር፥ ሕዝቡም ፀጥታው ተጠብቆለት እንዲሠራ ማድረግን ይጠይቃል:: አምራቹ የሕብረተሰብ ክፍልም ሆነ መዋዕለ ንዋዩን በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚያውለው ዜጋ የህግ የበላይነት የሠፈነበትና የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓት እንዲያገኝ ይፈልጋል::

እንደኢትዮጵያ ባለች ከሕዝብዋ ከ 85 በመቶ የሚሆነው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በእርሻ ላይ በተመሠረተ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ኑሮውን በሚመራበት ሀገር ውስጥ ደግሞ አርሶአደሩ የሚያርሰው መሬት ባለቤት መሆን/አለመሆኑ በእርሻው ምርት ላይ የማይታበል ተጽዕኖ አለው:: ኢትዮጵያችን ውስጥ ስለኢኮኖሚ ልማት ባጠቃላይ ስለእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ስንነጋገር ደግሞ ሌላ ተዛማጅ እንዲሁም አንገብጋቢ እየሆነ የሚመጣ ጉዳይ የውሀ ሃብት ልማት ጥያቄ ነው:: በሕዝባችንና በሀገራችን ላይ ትልቅ መቅሠፍት የሆነብን ድርቅ እንዳሁኑ ባያዘወትረን እንኳን እያደገ የመጣውንና ግሽበቱም እየቀጠለ ያለውን ሕዝባችንን በበቂ ለመመገብ እንድንችል በግድ ከመሬት ሥሪት ጥያቄ ጋር በተጓዳኝነት ሊመለስ ይገባዋል:: በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ያለውን የምግብ እጦት ለማስወገድ የወሀ ልማት ጉዳይን ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ዓበይት ጉዳዮች ጋር በተዛማጅነት ምላሽ መስጠት ይገባናል:: ዛሬ ሀገራችን ውስጥ እየተካሄደ ያለው እርሻ፥ ሙሉ ለሙሉው በሚያሰኝ ደረጃ፥ በተፈጥሮ

ዝናብ ላይ የተመሠረተ ስለዚህም አስተማማኝ ያልሆነ ነው፡፡ ይህን የማይታበል እውነት ተቀብለን እስቲ ደግሞ በቅደም ተከተል ሀገራችን ዛሬ ያለችበትን ሁኔታ ዘርዘር አድርገን እንመርምር፡፡

1. ገና ያልለየለትን ሆኖም ግን ለውጥን ለማምጣት ሀገሪቷ በምጥ ላይ የምትገኝበትን፤ ሕዝባችን በከፍተኛ ትንቅንቅ ውስጥ የገባበትን የሀገራችንን የፖለቲካ ሁኔታ ላንዳፍታ መለስ ብለን እናስተውል፥ በዚሁ ስር የሚካተቱትን የሀገር ኅላዌ፥ ፀጥታና መረጋጋት፥ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች፥ የህግ የበላይነትና የፍትኀ ርትዕ ጉዳይ፥ የግንቦቱ ምርጫ እንዴት ተካሄደ፥ ሲቪክ ማኅበረሰቡና የመደራጀት ጥያቄ ወ.ዘ.ተ. ምን ደረጃ ላይ ነበሩ? ዛሬስ?
2. የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ከተዛማጅ ዘርፎች ጋር አያይዘን ስንመረመር፥ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ/ት ለዕለት ምግብ ከመጨነቅ ማላቀቅ፥ እየበላ/ች አቅም አግኝቶ/ታ በጤናማነት እየሠራ/ች እየተሻሻለ/ችም ለመኖር ማብቃት እንደምን ይቻላል?
3. ማኅበራዊ ሁኔታዎችን በተለይም የትምህርትና የጤና ሁኔታዎችን፥ ሥራ አጥነትን፥ የህፃናትንና የልጆችን፥ የነፍሰ ጡርና እመጫት እናቶችን፥ የአሮጊቶችንና የሽማግሌዎችን እንክብካቤ ማግኘትን እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል?
4. የኤርትራ ጉዳይን አስመልክቶ በህወሃት/ኢሕአዴግና በሻዕብያ መሐከል የነበረው መመሣጠር፥እንዲሁም በሁለቱ መሐል የተደረገው ጦርነትና ከዚያም በኋላ የተደረጉት አደናጋሪ ስምምነቶችስ ከቶውንስ የሚዘነጉ ናቸውን?
5. ሀገራዊ የሆነ ሙያተኛ የጦር ኃይል ምሥረታ አስፈላጊነትና አንገብጋቢነትስ ጉዳይ?
6. የዲፕሎማሚያዊ ግንኙነታችን ለሕዝብና ለሀገር ጥቅም ወይንስ ለሌላ?

አዎን - የሃገራችን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ በቅጡ ሊመርመር የሚገባው መሰረታዊና መልስ የሚሻ ብርቱ ጉዳይ ነው፡፡

<u>የሀገራችን የወቅቱ የፖለቲካ ሁኔታ በኢሕአፖ አተያይ</u>

በአንድ በኩል በህወሓት መሪዎች ቁጥጥር ሥር ያለዉ ሌሎቹንም ተከታይና ተለጣፊ ቡድኖች ያካተተዉ የገዢዉ ክፍል አሁንም፡-

- የዘር/ብሔር-ብሔረሰብ/ ፖለቲካዊ መመሪያዉን እንዳነገበ ነው፤
- በአምባገነናዊነት በሥልጣን ኮርቻ ላይ ተንፈራጦ ለመቆየት ይፈልጋል፤
- ፀረ ዴሞክራሲ ፖሊሲዎቹን ተግባራዊ ለማድረግ ጨቋኝ፥ አማቂ፥ ፀረሕዝብና ያለጥርጥር ጎጂ የሆኑ ርምጃዎችንም በስፋት ፊት ለፊት እየወሰደ ነው፤

- የሕዝባችንንና የሀገራችንን አንድነት እያናጋ፥ ፀጥታዋንም በቀጣይነት እየጎዳ፥ እንዲያውም በሕዝባችን ብልህነት እየተጨናገፈበት ቆየ እንጂ በሕዝባችን መሐል የርስበርስ ፍጅት ለማነሣሣት እየጣረ ነው፤ ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቀዉ በሙስሌሞችና በክርስቲያኖች መሐከል በጅማ ከተማ ሰሞኑን የታዬዉ ዉዝግብ የዚሁ አካል ነዉ ፤

- የሰብዓዊ መብት ረገጣዉን በገፍና በይፋ እየፈጸመ፥ አለአግባብ እያሠረ፥ እያሠቃየ፥ በግፍ እየገደለም ነው፤

- ዘላቂ ሠላም ሊገኝ የሚችልባቸዉን ዉስጣዊ የፖለቲካ ችግሮችን በሠላማዊ ፖለቲካዊ መንገዶች የመፍታት ሥልቶችን ባለመጠቀሙ፥ እንዲያውም በተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎች ሲጠቆሙም በማጣጣሉና በማምከኑ ግጭቶችን እየጋበዘ ይገኛል፤

- አድሏዊ የሆኑ ፖሊሲዎችን ዛሬም እንደወትሮው ይሁን ብሎ እያራመደ፥ የዜግነት መብትን ባለማክበር ሀገራዊ ስሜትንም እያኮሰመነ ነው - እስከዛሬም የቆየው፤
- የሀገራችንን ሉዓላዊነት ለባዕዳን አሳልፎ በመስጠት ተግባሩ እየቀጠለ
- በሙስና እንደተበከለ በዝርፍያና በስርቆት እየበለጸገ ያለዉ በጸረ ሕዝብና አምባገነናዊ ተግባሮቹም በማንአህሎኝነት እየገፋ ነው ያለዉ፡፡ ይህ ያለጥርጥር በጠላት ጎራ የሚመደበው አረመኔያዊው አገዘዝን የሚያካትተው የጠላት ወገን ባንድ በኩል የተሰለፈበት ካምፕ ሲሆን

በሌላ በኩል ደግሞ በጣም ሰፊ የሆነዉ የከተማና የገጠር ነዋሪ ኢትዮጵያዊ፤ ማለትም ተማሪዎችን፤ ሥራ አጦችን፤ ሠራተኞችን (በአገልግሎት ሥራዎችም ላይ ጭምር የተሠማሩትን)፤አስተማሪዎችን፤ አርሶ አደሮችን፤ የቀድሞ ወታደሮችን፤ የቀድሞ ባለሥልጣኖችን፥ነጋዴዎችን፥ጭቁን የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያካተት የሕዝባችንን አብዛኛዉን ክፍል የያዘዉ ኢትዮጵያዊ ተሰልፏል፡፡

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በዚህ ጎራ የተሰለፈዉ በጣም ሠፊ የሆነዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በገዢዉ ክፍል ከተሰለፈዉ አነስተኛ ክፍል ጋር ተፋጥጧል፡፡ይህ ምልዓተ ሕዝብ ጉልህ በሆነ ድምጽ ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን ከነጠቁት እጅ መልሶ ለመዉሰድ በአንድነት ተነስቷል፡፡

- ሰብዓዊ መብቶቹ እንዲከበሩ በአንድነት ጠይቋል፡፡
- ዛሬም በአንድነት ቆሞ እየታገለ ነዉ፡፡
- ዛሬም ፍትኅን እንዲያገኝ ይጠይቃል፡፡
- በብሔረሰቦች መሐከልም ዘላቂነት ባለው መንገድ የእኩልነት መብታቸው እንዲረጋገጥ የአብዛኛው በሠፊው በሕዝባዊው ጎራ

የተካተተው የኅብረተሰብ ክፍል ጥያቄ ነዉ።

በሁለቱ ጎራዎች መሐከል ረዘም ላለ ጊዜ የነበረዉ ፍጥጫ ወደ መረረ ትግል ወደ ፍጥጫም አቅንቷል። በተለይ ዛሬ በሕዝብ ወገን ተሠልፎ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፥ ለሰብዓዊ መብት መከበር፥ ለፍትኅ፥ለእኩልነትና አንድነት እየታገለ ያለዉ የተወሰነ አነስተኛ ክፍል ብቻ ሣይሆን በርግጥም ሠፊ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ ምልዓተ ሕዝብ ነዉ።

ለተወሰኑ መሠረታዊ ጥያቄዎች ምልዓተ ሕዝቡና የተወሰኑ መደቦችንና የኅብረተሰቡ ክፍሎችን በመወከል የተደራጁት የፖለቲካ ሃይሎች በአንድ ሠፊ ክፍል አብረው ቢሰለፉም በማዕቀፉ ውስጥ ያሉት ሁሉም ንዑስ ክፍሎች በሁሉም ጉዳዮች ላይ አንድ ዓይነት አመለካከት እንደሌላቸው ደግሞ ያገጠጠ ያፈጠጠ እውነት ነው። ስለዚህ ምልዓተ ሕዝቡ በአንድ በኩል እጅ ለእጅ ተያይዞ በጋራ ለሚጠይቀዉ በአንድነት ይታገላል። በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ የኅብረተሰብ ክፍል የየራሱን ጠበብ ያለ ጥያቄ ሊያቀርብና በተለያዩ አጋጣሚዎች በተለያዩ መድረኮች ሊሻኮትና ሊሣሣብ ይችላል። ይሁን እንጂ ባሁኑ ወቅት ጎልቶ የሚታየው ሃቅ የሕዝቡ በጋራ ጥያቄዎቹ ላይ በአንድነት እያደረገው ያለው ትግል ነው።

- እንዲያውም በጣም ደስ የሚያሰኘዉ ደግሞ ዛሬም እንደወትሮዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነቱ በኢትዮጵያዊነቱ ተሣሥሮና አብሮም ነዉ ለመብቱ እየታገለ ያለዉ።ባለፉት 14 ዓመቶች ህወሓት/ኢሕአዴግ ከቻለ ለማጥፋት አለዚያም ለማናጋት ቢጥርም የሕዝቡ የአንድነት መንፈስ ህያዉ መሆኑ ተረጋግጧል። በዘር በሃይማኖት በአካባቢዎች ሳይከፋፈል ነዉ ሕዝቡ ለዲሞክራሲያዊ መብቱ በአንድ ላይ የወጣዉ የተነሣዉ እየተዋደቀም ያለዉ።
- ዛሬ ደግሞ ሌላዉ የምሥራች የሚያሰኘዉ ሁኔታ አዲሱ ወጣት ትዉልድ፥ ተረኛ የሆነውና በሀገራችን የወደፊት የለዉጥና የዕድገት ጉዞ ላይ ወሣኝ ሚና ሊጫወት የሚችል ትዉልድ፥ በትግሉ ዉስጥ ጎልቶ ጠንክሮና አምርሮ መነሳቱና መሳተፉ ነዉ። ይህ የሁኔታ ለውጥ ሁላችንም ስንመኘውና በተስፋም ስንጠብቀው የነበረ ክስተት ስለሆነ እሰየው የምሥራች የሚያሰኝ የሁኔታዎች ዕድገት ውጤት ነው።
- እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በሀገር ዉስጥና በዉጭም በጋራም ሆነ በተናጠል ባልተጠናከረ መንገድም ቢሆን የተደረገዉ ትግል ገዢዉን ኃይል እያጋለጠዉ ከሕዝብ እየነጠለዉ እየገዘገዘውና እያዳከመዉ መምጣቱ አጠራጣሪ አይደለም። በተለይ ኢሕአፓ በተናጠል ትግል አመርቂ የሆነ ውጤት አይገኝም ብሎ ባመነባቸው ጊዜዎች ሁሉ በኅብረት ትግሉ አማካይነት ትግሉን ለማስቀጠል ያለማሰለስ ጥሯል። በኢዴኃቅ፣ በኢተፖድኅ፥ በአማራጭ ኃይሎች፣ በኋላም በኢአግ አማካይነት ታግሏል፥ ከፍተኛ መሥዋዕትነትም ከፍሏል። በተለያዩ ኅብረቶች አማካይነት የተደረጉት ትግሎችና እንቅስቃሴዎችም አነሰም በዛ ሁሉም የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል። ድርጅቱ ዛሬም የህብረት አባል

በመሆን ላለፉት 3 ዓመታት ታግሏል፡፡

እርግጥ ነው - ለተወሰኑ ዓመቶች (ከ 1983 እስከ 1990 እንደ አዉሮጳዊያኑ አቆጣጠር ከ1991 እስከ 1998) ገዢዉ ኃይል ዉስጣዊ አንድነቱን ጠብቆ ጥንካሬዉን ሳያጣ ስለቆየ፥

ከሻዕቢያ ጋር የነበረዉንም የቃል ኪዳን ትስስርና ወዳጅነቱን ሳያናጋ ይዞ ስለቀጠለ፥ የባዕዳን ደጋፊዎችንም ያልተቋረጠ ወዳጅነት አግኝቶ ትብብራቸዉንና ርዳታቸዉንም በገፍ በማግኘቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደጨቆነና እንዳፈነ እንደናቀና እንዳዋረደ የሕዝባችንን አንድነት እንደቦረቦረና በተግባሮቹም እንዳናጋ የዉጭዉን ዓለምም እንዳታለለ ፈርጠም ብሎ አይሎ አምባገነናዊ አገዛዙን ለማስቀጠል ችሏል፡፡

በዚህ መሰሪ ባሕሪው ምክንያት ስለ ህወሓት(ህዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ)፥ስለማሌሊት(ማርክሲስት ሌኒኒስት ሊግ ትግራይ) ወይንም በዚሁ ድርጅት ስለ ተፈጠረዉ ኢህአዴግ ብዙዎቻችን አዲስ አይደለንም፤ እንዲያውም በሚገባ ከሁሉም ይበልጥ አበጥረንና አንጠርጥረን እናዉቀዋለንና የድርጅቱን ማንነት እዚህ በስፋት እንደገና ለመዘርዘር አንሻም፡፡ ሆኖም ግን ዛሬና ወደፊትም ለሚደረገዉ ትግል ጠቃሚም አስፈላጊም ስለሆነ አንዳንድ ገላጭና ዋና ዋና የሆኑትን ባህሪዎቹን ለማስታወስ ያህል፥ የተወሰኑትን በአጭሩ ብናነሣ ጠቀሜታ እንጂ ጉዳት አይኖረውም ብለን እንገምታለን፡፡

- አመራሩ ዛሬም ከትግራይ ወይም ከትግራይ ትግሪኝ ብሔረተኝነት አመለካከቱ አልተላቀቀም፡፡ ኢትዮጵያዊና ሀገራዊ የሆነ አመለካከትና አስተሳሰብ አልያዘም፡፡ ዛሬ ካላቸው ሠፋ ያለ በይነ ግብር አኳያ፤ ማለትም መኖሪያ ሥፍራዎቻቸውን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በማድረጋቸው፥ በፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ሥራዎቻቸው የተነሣ ካሏቸው ስምሪቶች፥ በኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውና ባካበቱት ሃብት ሥርጭት፥ አንዳንዴም በብሔረሰብ ዘለል ጋብቻቸው፥ የአስተሣሰብ ለውጥ ሊኖራቸው በተገባ ነበር፡፡ ነገር ግን አሣዛኝ በሆነ ደረጃ የህወሃት/ኢሕአዴግ ቁንጮዎችና ከሥራቸው ያሉት ከፍተኛ ካድሬዎቻቸውም ከተበከሉበት ጠባብ የብሔረተኛ አስተሣሰባቸው ዛሬም አልተላቀቁም፡፡
- ስለዴሞክራሲ ቢናገሩም አያምኑበትም፡፡ ዴሞክራሲን ኢትዮጵያ ውስጥ ለማስፈን እየሠራን ነው እያሉ ሰሚ እስከሚሰለች የሚናገሩት በተለይ ባዕዳን ርዳታ ለጋሾችን፤ እስከተቻለም የሚዘናጉ ኢትዮጵያዊያንንም ለማታለል የሚያጠልቁት ጭንብል እንጅ የዲሞክራሲን አስፈላጊነት በአስተሣሰብና በዕምነት ደረጃ አልተቀበሉም፡፡ ሰለዚህም ነው ዛሬም አምባገነናዊና ጸረ ዴሞክራሲያዊ ባህሪዎቻቸው ጎልተው የሚታዩት፡፡ አመለካከታቸውና ዕምነታቸው በተግባራቸዉ

በየዕለቱ ግልጽ እየሆነ መጥቷልና ነዉና ማንነታቸውን ለማወቅ ብዙም ምርምር አይጠይቅም::

- እነሱን እስከጠቀመች ድረስ አንጻራዊ የቆዳ ስፋት ያላት ኢትዮጵያን በቁጥጥራቸዉ ሥር ማቆየትና ሠፋ ያለ ሕዝብን ለመበዝበዝ የሚያስችላቸው ሁኔታን ማቆየት ቢፈልጉም ለሀገሪቱ ዘላቂ አንድነትና መረጋጋት ዛሬም አልቆሙም:: በኢትዮጵያ ስም ቢገዙም ዛሬም አንድነቷን ከማፍረስና ከማናጋት ዓላማዎቻቸዉ አልታቀቡም::
- ከህወሓት አመራር አባላት መሐከል ልዩነቶቻቸዉ አድገዉ የትግራይ ብሔረተኝነት ዕምነታቸዉ ጠንከር ያለዉ ወገን (የእነ ስዬ አብረሃ ገብሩ አሥራት ቡድን) የአቶ መለስ ዜናዊን በትግራይ ትግሪኝ ዕምነት የናወዘ ቡድን፤ ማለትም ትግራይን ሳይሆን በተለይ ኤርትራን ለማጠናከር በመጣር የተሰማራውን ቡድን አካሄድ ለመግታት በመነሣሣቱ፤ የእነ ስዬ -ገብሩ አሥራት ቡድን በህወሓትና በሻዕቢያ መሐል ለተፈጠረው ችግር፤ በኋላም በኢትዮጵያና በኤርትራ መሐል ለተፈጠሩት ልዩነቶች፤ ግጭቶች፤ጦርነቶች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል::
- ኤርትራዊነቱ የሚልጥበት አቶ መለስ ዜናዊ ህወሓት ዉስጥ የተፈጠረዉ ክፍፍልና ትግል አይሎና ጎልብቶ ተጻራሪዎቹ የሆኑትን በማሰርና በማግለል ከስብሃት ነጋና ሌሎኘ ተከታዮች ጋር ተቧድኖ በሌላኛዉ ቡድን ላይ የበላይነትን ይዟል::ምንም እንኳን ከዲሞክራሲያዊ አመለካከት አኳያ በሁለቱ የህወሓት ቡድኖች መሐከል የታየ ወይም የተከሰተ መሠረታዊ ልዩነት ባይኖርም መከፋፈላቸዉና ተከታትሎም ዉስጣዊ ገመናቸዉ በተከታዮቻቸዉ፤ እንዲሁም አፍነዉ ይዘዉት በቆዩት የትግራይ ህዝብ ባጠቃላይም በኢትዮጵያ ሕዝብ ዉስጥ እየታወቀ መምጣቱና ትኩረታቸዉም ወደ ዉስጥ ትግል መሸጋገሩ በሀገራችን ዛሬ ለተፈጠረዉ ለዉጥን ያረገዘ ሁናቴ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረጉ አልቀረም::

- ሻዓብያና ህወሓት ሌሎችን መሰል ቡድኖች ተባባሪአቸዉ አድርገዉ ከ1983 ጀምሮ በጠባብ ብሔረተኝነት ዕምነታቸዉ መሠረት የተቋቋሙና የተቃኙ የፖለቲካ ድርጅቶች በመፍጠርና በማጠናከር ህገ መንግሥት በማዉጣትና በሕዝቡ ላይ በመጫን ኤርትራን በማስገንጠል ፤ ክልሎችን በመመሥረት የኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነት ከመሠረቱ እንዲናጋ ተግተዉ ሠርተዋል::የሚወተውቱትን የብሔር ጥያቄም አልፈቱም - ይበልጡን አወሳሰቡት እንጂ::ስለዚህም የህወሓት መሪዎች ሌላዉ ገላጭ ባሕሪአቸዉ ጸረ አንድነት ነበር - ዛሬም ይኸው ነው::ዛሬም የአብዛኛዎቹ የህወሃት/ኢሕአዴግ መሪዎች ይኸዉ ጸረ አንድነት ባሕሪያቸው ነዉ ጎልቶ የሚታየዉ::
- እርግጥ ነው - የህወሓት አመራር የዉስጥ ክፍፍል በህወሓትና በሻዕብያ መሐከል የተፈጠረዉ የቃል ኪዳናቸዉ መፍረስና ርስ በርስ

ሽኩቻ ዉስጥ መግባታቸዉ ከዚያም በኢትዮጵያና በኤርትራ መኸከል የተደረገዉ ጦርነት በህወሓት ላይ አያሌ መዘዞችን አስከትሏል፡፡

- የህወሓት ማታለያዎችና ዉሸቶች ይበልጥ እየታወቁ አመራሩም እየተጋለጠ መጥቷል
- በህወሓት አመራር ዉስጥ የነበረዉ ክፍፍል ወደካድሬዎች፤ወደ ትግራይ ሕዝብ ወደ ሌላዉም የኢትዮጵያ ሕዝብ እየተዛመተ በመጣ ቁጥር መሪዎችም እየተናቁ መጡ፡፡
- ጦረኛነታቸዉ ከኢትዮጵያም አልፎ በባዕዳኑ ደጋፊዎቻቸዉ ፊት ተጋለጠ፡፡

አንድ ሊጤን የሚገባው ዓቢይ ጉዳይ ህወሓት ኢሕአዴግን በሥልጣን ላይ ለማስቀመጥም ሆነ የሥልጣን ኮርቻ ላይ ከወጣ በኋላ እነሱን በሥልጣን ላይ ለማቆየት የውጭ በተለይም የምዕራብ ሀገሮች የተጫወቱት ሚና ጉልህና ባመዛኙም ህዝባችንንና ሀገራችንን የጎዳ መሆኑ ነው፡፡

የህወሓት መሪዎች ለሠላም የቆሙ ለማስመሰል ብዙ ተናግረዉ ነበር፡፡የቀድሞዉን የኢትዮጵያን ጦር ሲያፈርሱና አባላቱንም ሲበታትኑ ማጠየቂያቸዉ "ለኢትዮጵያ ግዙፍ ወታደራዊ ሃይል አያስፈልጋትም"፥ ወደፊት የፖለቲካ ችግሮችም መፈታት የሚኖርባቸዉ በሠላማዊ መንገድ ነዉ፤ወ.ዘ.ተ. በማለት ነበር የውጭውን ኅብረተሰብ ለማጭበርበር የቻሉት፡፡ትኩረታቸዉ በወታደራዊ ተቋሞች ማጠናከር ላይ ሳይሆን በልማት ተግባሮች ላይ እንደሚሆንም ነበር ለምዕራባዊያን ለጋሾቻቸዉ ደጋግመዉ የሚገልጡት፡፡

የቀድሞውን ሠራዊት እንዲበትኑ ልዩ የገንዘብ ዕርዳታ ጠይቀዉ አግኝተዉም ነበር፡፡ሆኖም ግን ሻዓቢያ ከሚባለዉ የቀድሞ የቃል ኪዳን ወዳጃቸዉ ጋር በጦርነት ልዩነቶቻቸዉን ወደ መፍታት ሲሄዱ ሁለቱም ጦረኞች መሆናቸዉን በገሃድ ለማሳየት አላዳገተም፡፡እንዲያዉም የህወሓት መሪዎችም ሆኑ የሻዕቢያ መሪዎች በተለያዩ የሦስተኛ ዓለም ዉስጥ በጉልበት እየገዙ ካሉት ወታደራዊ ጁንታዎች የማይለዩ መሆናቸዉ በዉጭ ጋዜጠኞችና የፖለቲካ ተንታኞች ጭምር ሊወራ መቻሉ ደጋፊዎቻቸው ሊያለባብሱላቸው ይሞክሩ የነበረውን ሁሉ አስቸጋሪ አድርጎባቸዋል፡፡

ይመጻደቁበት የነበረዉን የሠላም አባወራነት ካባ ብዙ ሣያጌጡበት አዉልቆ ለመወርወር ተገደዋል፡፡ ዛሬ ደግሞ በውጭ ኃይሎች "አይዞህ " ባይነትና በተለይ የምዕራቡን ዓለም ድጋፍ ያስገኝልናል በሚል ስሌት ከሶማሊያ ጋር ጦርነት ለመጫር በመቅበጥበጥ ላይ ይገኛሉ ፡፡

የመለስ ዜናዊ ስብሓት ነጋ ቡድን የእነስዬ አብረሃን ወገን ሲከስና ሲያስር ጸረ ዴሞክራሲያዊነቱን ይበልጥ ለማረጋገጥ አስችሏል፡፡ ርስ በርሳቸዉ

እንኳን ተከባብረዉ ልዩነቶቻቸዉን በዉይይት ለመፍታት ብቃት እንደሌላቸዉና ለዴሞክራሲ መርሆዎች አክብሮት እንደማይሰጡ ለማያዉቋቸዉና ለሚከላከሉላቸዉ ጭምር ጸረ ዴሞክራሲ መሪዎች መሆናቸዉን በተግባራቸዉ አረጋግጠዋልና ይህንን ደካማ ባሕሪያቸውን ለማሳየት መቅለሉ የተቃዋሚዉን ሃይል ሥራ አግዟል።

ምንም እንኳን ዛሬ ከህወሓት/ኢህአዴግና ከደጋፊዎቻቸዉ ጋር እየተፋለመ ያለዉ መጠነ ሰፊ የሆነው የሕዝባችን ክፍል ቢሆንም፥በዚህ ጎራ የተካተቱ የኅብረተሰብ ክፍሎችና የፖለቲካ ሃይሎች በሙሉ ወጥነት ያለዉ አመለካከት ተመሣሣይ ጥቅምና ፍላጎት አንድ ዓይነት ራዕይ ያላቸዉ (ልዩነቶች የሌሉዋቸዉ) አይደሉም። በመኻከላቸዉ ልዩነቶች ስለአሉዋቸዉ ነዉ በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች በመደራጀት አሁን ደግሞ በተለያዩ ኅብረቶች ዉስጥ በመሰባሰብ የሚታገሉት። የሕወኃት/ኢሕአዴግን መልኮች የመገምገማችንን ያሕል ራሳችንንም መለስ ብሎ መመልከቱ ለወደፊት ይበጃልና ለመሆኑ ከሕዝብ የወገኑት ኅብረቶች ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምን ይመስላሉ?

ይቀጥላል።

<u>ማስታወሻ</u>

ይህ ጽሁፍ በኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ለአራተኛው የኢሕአፓ ጠቅላላ ጉባኤ የተዘጋጀ ሲሆን በአቶ ሰለሞን ገብረ ስላሴ ትብብር ለፍኖተ ዴሞክራሲ ሬዲዮ ዝግጅት በሚቀርብ መልኩ እንደገና ተዘጋጅቶና በፍኖተ ዴሞክራሲ ኢዲቶሪያል ቦርድ ታርሞ የቀረበ ነው።